# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች

ኢየሱስ የባሕሩን ወጀብ ጸጥ አሰኘው፡፡



ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest, Alastair Paterson

ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): Ruth Klassen

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2024 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።



አደገኛ አውሎ ንፋስ ሲነሳ ፤ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ በአንድላይ ጀልባ ውስጥ ነበሩ፡፡ አውሎንፋሱ ፤ የገሊላን ውቅያኖስ በአደገኛው መታው፡፡ የዚህ አይነት ወጀብ የመርከብ መሰበርና መስጠምን ሊያስከትል ይችላል፡፡

ወጀቡ ደቀመዛሙርቱን እጅግ አስፈራቸው። ወጀቡ ጀልባውን ሞላው፤ በውኃው ሸፈነው። በወጀቡ መሀል ግን ኢየሱስ በትራስ ተደግፎ ተኝቶ ነበረ። ደቀመዛሙርቱ እያለቀሱ እየሱስን ቀሰቀሱት፤ “ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ እየጠፋን ነው።”



ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን እንዲህ ብሎ ጠየቃቸው ፣ “እናንተ አናሳ እምነት ያላችሁ ስለምን ትፈራላችሁ?” ከዚያም እየሱስ የሚናወጠውን ወጀብ ጸጥ እንዲል አዘዘው፡፡



ከዚያም ነፋሱ ዝም አለ፤.................... ውቅያኖሱ ሰላማዊና ጸጥ ያለ ሆነ፡፡ ደቀመዛሙርቱም ተገርመው ፣ እንዲህ አሉ “ይሔ ማነው ? ንፋሳትና ውቅያኖስ ሳይቀር የሚታዘዝለት?”





ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፣ ኢየሱስ ሌላ የተጨናነቀ
ቀን ነበረው። ከ አምስት ሺህ የሚበልጡ ሰዎች
በምድርበዳ ሲከተሉት ነበረ። በእግዚአብሔር
ኃይል ፣ ያንን የሚያክልን ሰው በአንድ ሰው
ምሳ ብቻ ተጠቅሞ መገበው። ጊዜው ምሽት
ነበረ ፤ ኢየሱስም
ሁሉንም ሸኛቸው።

ደቀመዛሙርቱ እንኳን ሳይቀሩ መሔድ ነበረባቸው ፤ ኢየሱስም ጀልባ ውስጥ ገብተው ከእርሱ ፊት ሆነው ፣ የገሊላን ባሕር እንዲሻገሩ አደረጋቸው።





ሁሉንም ከሸኛቸው
በኋላ ፣ ሊጸልይ ፈልጎ
ወደተራራ ብቻውን
ወጣ፡፡ ምሽትም ሲሆን
፣ እዚያ ብቻውን ነበረ፡፡



በሃይቁ ውስጥ እያሉ ፣ ደቀመዛሙርቱ
አውሎንፋስ ተያዙ፡፡ ለሰዓታት
እየቀዘፉ ቢቆዩም ፣ ወጀቡ
ውኃውን ማቋረጥ እንዳይችሉ
ከለከላቸው፡፡ ደቀመዛሙርቱ
ይሔንን አያውቁም
ነበረ፤ ነገር ግን
በታላቅ መደነቅ
ሆነው ውስጥ
ነበሩ፡፡



ከሶስት እስከ ስድስት ባለ
የንጋቱ ሰዓት ፤ ነፋሱ
ውኃውን እያናወጠው
ባለበት ሰዓት ፤
ደቀመዛሙርቱ በፍርሃት
እንዲሞሉ ያደረጋቸውን
አንድ ነገር አዩ፡፡ እየጮሁ
“ምትሃት ነው!” አሉ፡፡
ነገር ግን በውኃ ላይ
እየተራመደ ወደ እነርሱ
ይመጣ የነበረው ጌታቸው
እና አለቃቸው የነበረው
ኢየሱስ ነው፡፡

ኢየሱስም “አይዟችሁ!” አላቸው። “እኔ ነኝ ፤ አትፍሩ።” ጴጥሮስም መለሰ፣ “ጌታ ሆይ ፣ አንተ ከሆንክ ፣ በውኃው ላይ ተራምጄ እንድመጣ እዘዘኝ።” ኢየሱስም አለ፤ “ና!” ወዲያውም ፣ ጴጥሮስ ከጀልባ ወጥቶ ውኃው ውስጥ ገባ እና ወደ ኢየሱስ ተራምዶ ሔደ።





ነገር ግን ነፋሱ ሲንቀሳቀስ
አይቶ፣ ጴጥሮስ ፈራ ፣
ይሰጥምም ጀመረ።
እንዲህም ሲል ጮኸ
“ጌታ ሆይ ፣ አድነኝ!”

በፍጥነትም ፣ ኢየሱስ እጆቹን ዘርግቶ ጴጥሮስን ያዘው፡፡
እንዲህም አለው ፤ “ ኦ! አንተ እምነት ያነሰህ ስለምን
ትጠራጠራለህ?” ከዚያም ፣ ጴጥሮስና ጌታ ኢየሱስ ወደ
ጀልባው ውስጥ ሲገቡ ነፋሱ ጸጥ አለ፡፡



ከዚያም በጀልባው ውስጥ የነበሩ
መጡና ለኢየሱስ ሰገዱለት፡፡
እንዲህም አሉት “አውነትም አንተ
የእግዚአብሔር ልጅ ነህ”



ኢየሱስ የባሕሩን ወጀብ ጸጥ አሰኘው፡፡

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ማቴዎስ 8፣ ማቴዎስ 14 ፣ ማርቆስ 14 ፣ ሉቃስ 8

**“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”**
**መዝሙረ ዳዊት** 119:130

# መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16